# መኖርያም መቀበርያም ያጣ ሕዝብ

“ምነው ካልጠፋ ቦታ?” የሚል ጥያቄ ሊነሳ እንደሚችል ባውቅም ለምን መቃብር ተደግፌ ይህንን ጽሁፍ መጀመር እንደተገደድኩ ተናግሬ ወደ አሰብኩበት አብሬአችሁ አዘግም ዘንድ መረጥሁ።

አዱ ገነት በምንላት ከተማችን ዛሬ ትኩስ ሬሣ ሊቀብር የመጣ ትናንት የቀበረው ላይ ይጸዳዳል። አሮጌ የቀብር ቦታ ፈንቅሎ ትኩስ ሬሳ ሲያስቀምጥ ለነገ የርሱ አፅም ተረኛ መሆኑን ልብ አይልም። እስኪ አስቡት መቃብር ላይ መጸዳዳት። የሙታን አፅም እንኳ የዘለዓለም እረፍቱን ማግኘት የማይችልበት አገር እየሆነች ነው። አሁን ደግሞ የቀብር ስፍራ ለአብያተ ክርስትያናት የገንዘብ ማስገኛ ቦታም ጭምር ስለሆነላቸው የመቃብር ቦታና የሀውልት ማሰርያ ዋጋው እንደ ከተማው መኖርያ ቦታ የናረ ነው። ሆኖም ታድያ ለቀብሩ ሥፍራና አንዳንዶች ለሐውልት ማሰሪያ ገንዘብም ጭምር ይውሰዱ እንጂ ለጥበቃው የሚያደርጉት ነገር የለም። ከአንዱ ሀውልት በተሰረቀው ሌላኛው እየተሰራ ገንዘብ እንደሚገኝ ሲነግሩዋቸውም ከጉዳይ አይቆጥሩትም። ስለዚህ ሀውልቱ ከተሰራና ከተመረቀ በሁዋላ እስከ አርባው ድረስ ጠብቆ “...ምን ማድረግ ይቻላል?” በማለት ፈርሶ እስኪያልቅ ማየት ነው። ከዚያም በላይ ደግሞ የመቃብር ቦታዎች ወደ ጎንጻነት ተለውጠው ደብዛቸውም የጠፋ ብዙ ሥፍራዎች አሉ።

እኔ የተቀመጥኩት ግን ከጎልፍ መጫዋቻ ሜዳ የሚስተካከል በሚገባ የተከረከመ ሳር አሻግሬ እያየሁ በአነስተኛ የእምነበርድ ላይ በፈረንጆች አቆጣጠር በ 1948 እና በ 1952 ዓመተምህረት ከዚህ ዐለም በሞት የተለዩ ባልና ሚስቶች አፅም በክብር ከአረፈበት ቦታ ነው። ስንተኛው ትውልዶች እንዳኖሩበት ባላውቅም መጠውለግ የጀመረ አበባና ሽንጥ የተደረገ ነድዶ የጠፋ ሻማ ይታዩኛል። የቀብር ሥፍራ ታላቅ የመታሰብያ ቦታ መሆኑ የገባኝና ከአለነው ጋር ያለው ትሥሥርና ቅርበት ታላቅ መሆኑን ያስታወሰኝና ቆም ብዬ እንዳስብ የተገደድኩበት ወቅት ነበር። ለመጻፍ ያነሳሳኝ ምክንያት ግን ወዲህ ነው።

አንድ ወዳጄ ከአገሩ በወጣ በሩብ ምዕተ ዓመቱ ሚስቱንና ሁለት ልጆቹን ይዞ አገር ቤት ደርሶ ከተመለሰ በሁዋላ ያወጋኝ ታስቦኝ በአእምሮዬ ተሰንቅሮ የቀረው *“መኖርያም መቀበርያም ያጣ ሕዝብ”* ያለው በዚህ የመቃብር ሥፍራ ቢጮህብኝ ከነበርኩበት ሳልርቅ ጫር ጫር ላድርግ ብዬ ነው መቃብር መሀል አረፍ ማለቴ።

ይኸው ወዳጄ አንዳንዴ በጨዋታ መሀል አባቱ የታወቁ ኢንጅነር እናቱም የቢራ ፋብሪካ ባለሀብት እንደነበሩ በኩራት ይነግረን ነበር። አሁን ሁለቱም በህይወት የሉም። እንዴት እንዳሳደጉትና እንደ አስተማሩት ሲናገር እጅግ ይመስጣል። በራስ መተማመንና ሰርቶ ሰው መሆንን ከማንም በላይ እንዳስተማሩት ሲናገር ኮራ ብሎ ነው። “.... ከኢንጅነር አባትና ባለጠጋ እናት ተወልዶ ታድያ እንዴት ይሁን ትሉ ይሆናል?...” ነገሩ እንዲህ ነው። ኢንጅነር አባቱ በዚያ ጊዜ አጠራር ‘የጭቃ ረጋጭ’ [*በዘመነ ብሎኬት ለተወለዳችሁ ጭቃውን ወደ ግድግዳነት የሚቀይሩ ባለሙያዎች ጭቃ ረጋጭ ይባላሉ*] ነበሩ እናቱም ጠላ ነጋዴ። ሙልጭ ያሉ የንዋይ ድሆች የራዕይ ግን ባለጠጋዎች ነበሩ። በመሆኑም ጥሩ ልጆች አሳድገው አስተምረው አልፈዋል።

እንደ ወጉ እናትና አባቱ መቃብር ላይ አበባ ሊያኖር በአግባቡ ሊሰናበታቸውና ለልጆቹም ታሪኩን ሊነገር አስቦ ወደ ቤተክርስትያን ለመሄድ ያደረገው ሙከራ አልተሳካም። ለመታሰብያ ብሎ መጠነኛ ሀውልት ለማሰርያ የሚሆን ገንዘብ በወቅቱ ልኮ ፎቶግራፍም በመረጃነት ተልኮለት ነበር። አሁን ሁሉም የሉም። በምትኩ ትልቅ ጎንፃ ቆሞአል።

ይህን ሲነግረኝ ዐይኑም አፍንጫውም እኩል ያነቡ ነበር። ተጫዋች ሰው እንዲህ ሲንሰቀሰቅ አንጀት ይበላል። “....ቆሜ አላስቀበርኳቸውም ከድህነት እልፍ አላሉም። አሁን የልጅ ልጆች ይዤላቸው ዘራችሁ በዝቷል ልላቸው ብሄድ የሉም። “...ኩርማን መሬቴን የሚከለክለኝ የለም በላቤ አድራለሁ!” የሚለው አባቴ ኩርማን መሬት ተከልክሎ አፅሙ ተበትኖአል። የአገሩን አፈር ይቅመስ የሚሉት ነገር ፌዝ ይመስለኛል ዳኜ። የሚቀመስ የአገር መሬት የለም። ሕዝባችን መኖርያም መቀበርያም ነው ያጣው እኮ!!...” እያለ ሀዘኑ አዲስ የሆነበትን ያህል ይንሰቀሰቅ ነበር። መለስ አድርጎም ደግሞ “.... ብቻ ነገሩን ነው እንጂ ጭቃ ሲያቦካ ለኖረ፣ ጭቃ ሲለጥፍና ሲለስን ለኖረ ሰው አፈር እኮ ብርቁ አይደለም። ለኛ እንጂ ያረፉበትን አውቀን እናመሰግናለን ልንላቸው፣ ሁሌም በሀሳባችን ውስጥ አላችሁ ልንላቸው የምንሻ የተበደልን እነርሱማ አልፈዋል። ተወው ዳኜ ዘመድ ካለህ አምጣ፣ ወደፊት የቅርብ ዘመድ ሲሞት ሬሣ ስፖንሰር አድርገን እዚሁ አስቀብረን በየጊዜው እንጎበኛቸዋለን። መቃብር ይከበራል ማንም አያፈርስብንም...” ያለው ታስቦኝ ነው።

ሰርቶ መኖር ባለመቻሉ፣ በነጻነት መግባትና መውጣት ቅንጦት በመሆኑ ወጣቶቻችን እየሄዱ መሞትን መርጠው ግማሹ ለአሳ፣ ቀሪው ለአንበሳ እራት ይሆናሉ። እኒያ ውብ ወጣት ሴቶች እህቶቻችንና ልጆቻችን የሴት ክብራቸው መጫወቻ፣ የአረቡ የቀማኛው የወሲብ ማርኪያ ሆነው የተረታ ገላቸውን ተስፋ በቆረጠ አእምሮ ወዲያ ወዲህ ያደርጉታል። እንዲያም ሆነው ህይወታቸው ስታልፍ አገር አልባ ተቆርቋሪ አልባ ናቸውና ክርስትያኖቹ የሙስሊም ስም ተለጥፎባቸው ወደማይታወቀው መቃብር ይወርዳሉ። ለዚህ ነው “መኖርያም መቀበርያም የጠፋው ሕዝብ” ማለቱ አእምሮዬን የነካው።

ወዳጄ በዚያ አላበቃም ነበር እናም ሳግ እየተናነቀው “.....የትግሬ ተገንጣዮች (ወያኔ ማለት አይወድም ተገንጣይ ድርጅት የሚለውን ይሸፍንላቸዋል ይላል) ብቻም አይደሉም እኮ እናትና አባትም ከፍቷል። ልጅ “..መንገላታቱ በዛብኝ ልመለስ..” ብላ ስትለምን እንኳ “ምን ልትሆኚ ነው የምትመጪው?” ይላሉ። ልጆቻቸውን ለመሸጥ ወደሁዋላ የማይሉ ግራ የገባቸውና ተስፋ የቆረጡ ወላጆችም እኮ ሞልተዋል። ያለ እድሜአቸው ጡረተኛ ሆነው ልጆች ኤክስፖርት የሚያደርጉ ወላጆችም እኮ አሉ አረ እባክህ ተወኝ። አረ እባክህ ተወኝ ድህነት ያዋርዳል፣ ድህነት ያሳንሳል ......” ማለቱ እውነት እውነት እንድለው አድርጎኛል።

አዲስ አበባ ውስጥ ችግሩን ጉስቁልናውን ችለው ይኖሩ የነበሩ ሰዎች መኖርያቸው እየፈረሰ የዘመኑ ገዢዎች ባለሀብቶች እየተቀራመቱት ነው። “...ከዚህ በመለስ ይፈርሳል..” ማለትን እንጂ “... የተፈናቀላችሁ እዚህ ትሆናላችሁ ...” በማይሉ ወራሪዎች ቂም የተያዘበት የአዲስ አበባ ነዋሪ መኖርያ እየተነፈገው ነው። ስለመቀበርያ ስናወራ መኖርያውም እየጠፋ መሆኑን ልብ ያለማለት እንደምን ይቻለናል? ስለዚህ ወዳጄ እንኳን የወላጆቹ መቃብር ይኖርበት የነበረውም ሰፈር ፍርሷል። ለነገሩማ ወገኖቼ በአለፈው ሩብ ምዕተ ዓመት ኢትዮጵያም ከወደ አናትዋ ፈርሳብን ስንጥቅዋ እየሰፋ አይደለም? ልጆችዋም እንደሚደረመሰው መቃብር፣ እንደሚፈርሰው ጎንፃ እንደምትፈርሰውም አገር እየተደራጀን መፋረስ ይዘናል። እስቲ እርግማኑ እንጂ ምርቃቱ አልይዝ ቢለንም፣ መጪው ዘመን ደግሞ የመደራጀትና የመገንባት የማሸነፍና የመሰባሰብ ይሁንልን ብዬ ልለያችሁ።

መልካም አዲስ ዘመን!!

ዳኛቸው ቢያድግልኝ
biyadegelgne@hotmail.com